# ለመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ የሚደረገው ትግል በሽፍጥና በማምታታት አይከስምም

# ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት (መድረክ)

## የግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ምርጫን በሚመለከተ የተሰጠ መግለጫ

የ2002 ዓ.ም አጠቃላይ ምርጫ ጉዳይ ከመታቀዱ ዓመታት አስቀድሞ የመድረኩ አባል ድርጅቶች፣ ከዚያም መድረኩ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ፤ በሀገራችን ምርጫ ነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒ እንዳይሆን ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ላይ ከገዢው ፓርቲ ኢህአዴግና ከመንግሥቱ ጋር ለመነጋገር፣ ለመደራደር ተደጋጋሚ ጥያቄ በማቅረብ ከፍተኛ ጥረት አድርገው እንደነበር የሚታወቅ ነው። በተለይም ኢህአዴግና መንግሥቱ ከሁለት ዓመት በፊት በተካሄደው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ ላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለመሳተፍ ያደረጉትን ጥረቶች ከንቱ ከማድረጋቸውና በአባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ላይም ከሰነዘሩት ጥቃት የተነሳ በሀገራችን ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ከፍተኛ ችግር ላይ እንደወደቀ በመገንዘብ ይህንን አደገኛ ሁኔታ በውይይትና ድርድር ለመቀየር፤መድረኩ እልህ አስጨራሽ ጥረቶችን ሲያደርግ እንደነበር ማስታወስ እንወዳለን። የዚህ ጥረታችን አካል የነበረው ከዓለም አቀፍ ለጋሽ አገራትና ድርጅቶች በጉዳዩ ላይ ድጋፍ ለማግኘት ያደረግናቸው ጥረቶች ይህ ነው የማይባል ፋይዳ ያለማስገኘታቸውንም አስታውሶ ማለፍ ተገቢነት አለው።

ለዚህ ሀገራዊና ሕዝባዊ ኃላፊነት ለተላበሰ ጥረታችን ገዢው ፓርቲና መንግሥቱ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም" እንዲሉ ሆነና ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎች ሳይስተካከሉ መቅረታቸው በእጅጉ ያሳሰበን ጉዳይ ነበር። በአንፃሩም ኢህአዴግ ጭላንጭሉንም የፖለቲካ መድረክ ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር ቅድሚያ ዝግጅት በማድረግ ተግባሮች ላይ ተሰማርቶ ቆይቷል። ከነዚህም መሃከል እንደ የምርጫ ሥነ ምግባርና የፀረ ሽብርተኛ አዋጆችን የመሳሰሉ ሕጎችን በመደንገግ የተቃውሞ ፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን ሕግ ጣሳችሁ ወዘተ በማለት ለመወንጀል ቅድሚያ ዝግጅት እየደረገ እንደበር የተገነዘብነው ጉዳይ ነበር።

በሀገሪቱ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች መሠረት ለነፃ፣ ፍትሐዊና ተዓማኒ ምርጫ አስፈላጊ ሁኔታዎች ያልተሟሉበት ሁኔታ መኖሩን መድረክ ቢገነዘብም፣ በሂደት ሊሻሻሉ በሚችሉ

ሁኔታዎች ላይ የመደራደር ጥረቶችን እያደረገ በ2002 ዓ.ም አጠቃላይ ምርጫ ውስጥ ገብቶ የመንቀሳቀሱን ተገቢነት እንደ አማራጭ በመውሰድ ተንቀሳቅሷል። ሆኖም ይህ በመድረኩ የተመረጠው በምርጫው እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ሆኖ መሠረታዊ የሆኑትን የሂደቱን ችግሮች በውይይትና በድርድር እያስወገዱ የመቀጠሉ ስልት በኢህአዴግ ወገን ባለመስተናገዱ የምርጫው አፈፃፀም በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንደሚወድቅ ግምት ነበረን። እንደገመትነውም ችግሮቹ በሁሉም የምርጫ እንቅስቃሴ እርከኖች የተከሰቱና በመላው ሃገሪቱ የተንሰራፉ ስለነበሩ ከዚህ አካባቢ ይልቅ በዚህኛው ይሻላል የሚባል ሁኔታ ያለመኖር በዚህ ምርጫ ላይ ኢህአዴግ ቁጥራቸው የበዛ ፓርቲዎችን በውሸት ውድድር ውስጥ ሲያሯሯጥ ቆይቶ በመጨረሻው አሸነፍኩ ለማለት መወሰኑን ተገንዝበናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ መድረኩ በግንቦት 15 ቀኑ ምርጫ ውድድር ውስጥ የገባው ሕዝባችንን ተገኑ አድርጎ በሰላማዊ አግባብ የሀገሪቱን ሕግጋት አክብሮ በሐቀኝነት ለመወዳደር ነበር። ለዚህም ያለ የሌለ አቅሙንና ዕውቀቱን ሁሉ በማዋል ብዙ ሠርቷል፤ ለፍቷልም። ለዚህም አብነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከኢህአዴግ ቀጥሎ ከፍተኛውን ቁጥር (489) ዕጩዎች እና ለክልል ሸንጎዎች ደገሞ 934 ዕጩዎችን በማቅረብ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረጉ ነው። በዚህ እርምጃው ለሕዝብ በአደባባይ ቃል በገባው መሠረት ግልጽ አማራጭ አጀንዳ ቀርፆ በምርጫው ተወዳድሮ አሸንፎ በመውጣት ማራጩን ሕዝብ ለሥልጣን ባለቤትነት ለማብቃት ተንቀሳቅሷል። ለምርጫው በቂ ዝግጅት በማድረግም መድረኩ ሀገራዊና ሕዝባዊ ኃላፊነትን ተወጥቷል። በሌላ ወገን ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ ይሆናል በማለት ሲምሉና ሲገዘቱ የነበሩትን ኢህአዴግንና የእርሱ የብቻው ፍጡር የሆነውን ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን በራሳቸው ሜዳ መድረኩ ፈትኗቸው በሰፊው ሕዝባችን ፊት ባዶ መሆናቸውን አጋልጧቸዋል፤ለሀቅ በሀቅ የማይሰሩና የማይንቀሳቀሱ የውሸትና የአስመሳይ ተግባራት ተቋማት ስለመሆናቸው ለአንዴና ለሁሌም እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል። ይህንን ስንል ያለ መረጃ አይደለም ኢህአዴግና የምርጫ አስፈፃሚ ተቋሙ የሕዝብና ሀገራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ብቃትና ፍላጎት አጥተው በሕገ ወጥነት የግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ምርጫን ሂደትና ክንዋኔ ከመነሻው ጀምሮ ችግር ላይ ስለመጣላቸው የሚከተሉትን ማሳያዎች በዋቢነት እንጠቅሳለን።

1. የመራጭ ምዝገባ ሂደትን ለኢህአዴግ ወገንተኛ በሆነ አኳኋን ማከናወን፣
2. የዕጩነት ምዝገባን ሂደት አወዛጋቢና ለኢህአዴግ ወገንተኛ በሆኑ ሁኔታ ማከናወን፣

3. የመድረክን የምረጡኝ ቅስቀሳ ከፍተኛ ችግር ላይ መጣል። ይህ ሁኔታ የሰብሰባ አዳራሾችንና ሜዳዎችን ከመከልከል አልፎ የተጠሩትን ስብሰባዎች ወረበላዎችን አሰማርቶ ማስበጥበጥ፣ ለቅስቀሳ የሚውሉ መሣሪያዎችን መንጠቅና መዝረፍ፣ በትራንስፖርት መገልገያ በምንጠቀምባቸው መኪናዎች ላይ አደጋ ማድረስ፣ መተላለፊያ መንገድ መዝጋት እና ሌሎች ህገ-ወጥ ተግባራትን መወጠናቸው መፈፀማቸውና ያለማስቆማቸው፤

4. የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ጊዜን ማጥበብና በቅድሚያ ምርመራ እርምጃዎች መሰናከል። እንደዚሁም የምረጡኝ ቅስቀሳ እንቅስቃሴዎችን በዜናነት ሆነ በዘገባ መልክ ለሕዝቡ ያለማድረስና ሁኔታውን ስርዓት ያለማስያዝ፤

5. በዕጩ ተወዳዳሪዎቻችን ላይ የተለያዩ ተጽዕኖዎችን በማሳርፍ ከዕጩነት ራሳቸውን እንዲያገሉ ዘመቻ መካሄድና ይህንን ያለማስቆም፤

6. የሀገሪቱን ሕገ መንግሥት የምርጫ ሕግና የምርጫ ሥነ ምግባር ሕግን በመተላለፍ ኢህአዴግ መድረክ ላይና በአመራሮቹ የሰነዘረው የስም ማጥፋትና የውንጀላ ዘመቻ ይህንን ሁኔታ ስርዓት ያለማስያዝ፤

7. የመራጩን ነፃነት በመግፈፍ ኢህአዴግ 1 ጠርናፊ ለ5 ተጠርናፊ የሚል ስልት ተጠቅሞ እኔን ምረጡኝ በማለት በሕገ ወጥነት ከሕዝብ ፊርማ በማሰባሰብ እንቅስቃሴው ማራጩን ሕዝብ ማወኩ እየታወቀ የምርጫው ሂደት እንዲቀጥል መደረጉ፤

8. አርሶ አደሩን ኢህአዴግን ካልመረጥክ የእርዳታ እህል አታገኝም፣ ሴፍቲኔት አትታቀፍም፣ የግብርና ዓብዓቶች አታገኝም በማለት ወጣቱን የሥራ ዕድል አይኖርም በማለትና የመንግሥት ሠራተኛውንም የሥራ ዋስትና አይኖርህም በማለት የመራጩን ሕዝብ ህልውና ስጋት ውስጥ ለመክተት የተደረገው ነውረኛ እንቅስቃሴ ሳይገታ የምርጫ ሂደቱ መቀጠሉ፤

9. በገጠሩና በከተማ በየመንደሩ መራጩን ሕዝብ ለማሸማቀቅ የተሰራጨው የታጠቀ ሠራዊት በመራጩ ሕዝብ ላይ ያሳደረው የስነ ልቦና ተጽዕኖ እና እንግልት መኖሩ፤

10. የመራጮች ካርዶችና የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በህዝብ ውስጥ በብዛት ተሰራጭተው መገኘትና ኢህአዴግን አይምረጡም ተብለው ከሚጠረጠሩት ላይ የምርጫ ካርድ በመሰብሰብ መራጩ ሕዝብ የኢህአዴግ ካድሬዎች ተጽእኖ ማሳረፋቸው ገሃድ ሆኖ መቀጠሉ፤

11. ከአንድ በላይ የምርጫ ካርድ ለአንድ የኢህአዴግ አባል በመስጠት፣ አንድ መራጭ ከአንድ ጊዜ በላይ ድምጽ እንዲሰጥ ሁኔታውን ማዘጋጀት፣

12. መድረክ የመደባቸውን የምርጫ ጣቢያ ተወካዮች በደንቡ መሠረት ተቀብሎ ባለማስተናገድ ምርጫው ያለተወካይ እንዲካሄድ ስልት መቀየስ፤

**በምርጫ ዕለት የተከሰቱ ሕገ ወጥ ሁኔታዎች በመርጫው ዕለት በኢህአዴግ የተፈፀሙ ሕገ-ወጥ እና ሥርዓት አልባ እርምጃዎች፣ ተዘርዝረው የማያልቁ ቢሆኑም ለአብነት ያህል ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን።**

- የመድረክ ተወካይ ወደ ምርጫ ጣቢያ እንዳይገባ በታጠቁ ሠራዊት አባላት ማሳገድ፣ ተወካይ በሌለበት የምርጫ ሰነዶችን መክፈትና ቀድመው የተሞሉ የድምጽ መስጫ ኮሮጆዎችና የተቀደዱ እሽጎች ላይ እርምጃ እንዳይወሰድ ማድረግ፤
- የምርጫን ሕግ የጣሱ እርምጃዎችን በማሳረም ስርዓት ለማስያዝ የሚጥሩትን የመድረክ ተወካዮች መደብደብ፣ ማሰር፣ ከጣቢያ ማባረርና በመመሪያው መሠረት ቅሬታ እንዳያስመዘግቡ ቅጽ መከልከል፤
- ኢህአዴግ 1 ለ5 በማለት ያደራጃቸውን መራጮች በቡድን ወደ ድምጽ መስጫ ክፍል በማስገባት በኢህአዴግ ካድሬዎች መመሪያ እየተሰጣቸው ንብ ላይ ምልክት እንዲያደርጉ ተጽእኖ በማሳረፈ የምርጫን ምስጢራዊነትና የዜጎችን ነፃነት የገፈፈ እርምጃ መውሰድ፣
- በየምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የቀበሌ አስተዳዳሪዎችና፣ የሥነ-ሥርዓት አስከባሪዎች ኢህአዴግን ለማስመረጥ ኮሮጆ እየሞሉ መገኘታቸው፤
- አስተዳዳሪዎችና የምርጫ አስፈፃሚዎች መራጩ ሕዝብ ኢህአዴግን እንዲመርጥ ማስገደዳቸውና ይህንን በማድረግ ባልተባበሩት ላይ ደብደባ መፈፀማቸውና ማሰራቸው፤
- አንድ መራጭ ብዙ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተሰጥተውት በኮሮጆ እንዲከት ማስገደድ፤
- ሕዝብ ለመድረክ ድምጽ ለመስጠት የሞላውን ኮሮጆ በማስወገድ የኢህአዴግ ምልክት (ንብ) በሕገ-ወጥነት የታጨቀበትን ኮሮጆ መተካት፤
- በድምጽ ቆጠራው ወቅት የምርጫ አስፈፃሚዎችን ኢህአዴግን ለማስበለጥ ስልት ይዘው መንቀሳቀሳቸውና በዚህም ምክንያት የተቆጠረው በየቀበሌው የመራጭ ድምጽ ለመምረጥ ከተመዘገበው ሕዝብ ቁጥር በላይ መሆኑ እየታወቀ መታለፉ፤
- የምርጫው ክንዋኔ ሕገ-ወጥ መሆኑን የተገነዘቡ የመድረክ ተወካዮች፣ በምርጫው ማጠናቀቂያ ቃለ-ጉባኤ ላይ መብታቸውን ተጠቅመው ላለመፈረም በመወሰናቸው

ምክንያት ለከፍተኛ እንግልትና ድብደባ መዳረጋቸው እና ከጣቢያው ታግተው ያሉትን ያለምግብና ልብስ እንዲያድሩ መደረጋቸው እና ከጣቢያው መውጣት የቻሉትንም አስገድዶ ለማስፈረም እያሳደዷቸው መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው።

## በምርጫው ዕለትና ከዚያ ወዲህ ባሉት ቀናት ውስጥ በተወካዮቻችን ላይ በስፋት ጥቃት የተሰነዘረባው መሆኑ ለምሳሌ፡-

1. በጥይት ተመተው የቆሰሉ፣
   - 1.1 አቶ መንግስቱ ወርቁ በ15-09-02 በምዕራብ ሸዋ ጀልዱ ወረዳ
   - 1.2 አቶ በቀለ ጎሳ በ15-09-02 በምዕራብ ሸዋ ኖኖ/ሸናን ወረዳ
   - 1.3 አቶ ግርማ አበበ በ15-09-02 በምዕራብ ሸዋ ደንዲ(ቁ.01) ወረዳ
   - 1.4 አቶ ታዬ ሽቶ ጉርሜሳ በ15-09-02 በምዕራብ ሸዋ ደንዲ(ቁ.01) ወረዳ
   - 1.5 አቶ በላይ ደምሴ መርሻ በ15-09-02 በምዕራብ ሸዋ ደንዲ(ቁ.01) ወረዳ
   - 1.6 አቶ ተመስገን ፈቃዱ ፋንታ በ16/09/02 ምዕራብ ሸዋ ማደቀኝ ወረዳ
2. በጩቤ የተወጉ፣
   - 2.1 አቶ ጉልማ ገመቹ የብሳ በ15/09/02 ምዕራብ ሸዋ ኖኖ ወረዳ
   - 2.2 አቶ አዮቤ ዱካ በ15/09/02 ምዕራብ አርሲ አዳባ ወረዳ (ዲንሾ)

ከነዚህ በመግሪያ ጉዳት ከደረሰባቸዉ ተወካዮቻችን በተጨማሪ በድብደባ ጉዳት የደረሰባቸው ተወካዮቻችን በብዙ ሺዎች ይቆጠራሉ። እንደዚሁም በምዕ/ሸዋ ዞን ደንዲ (ቁ 01) ወረዳ የምርጫ ኮሮጆን የቀበሌ ሊቀመንበር ይዞ ሲሸሽ ተወካያችን በሕግ እያለ የድረሱልኝ ጩኸት ሲያሰማ ለእርዳታ የወጣው አቶ ተስፋዬ ሰርቤሳ በተፈጠረው ግርግር መሃከል በቀበሌው ሊቀመንበር በተተኮሰ ጥይት ሕይወቱን አጥቷል።

ከፍ ብሎ ለማሳያነት ያቀረብናቸው በተወካዮቻችንና በጠቅላላው መራጩ ሕዝብ ላይ የተሰነዘሩት የጥቃት እርምጃዎች የሚያሳዩት ኢህአዴግና መንግሥቱ በመድረክና አባላቱ ላይ በምርጫ አማካኝነት መጠነ ሰፊ አፈና አውጀው እንደነበረ ነው። የአፈና ዘመቻ በምርጫ እለት ተባብሶ የኢህአዴግ ካድሬዎች፣ አስተዳደሩና የታጠቀው ሠራዊት በመላ መራጩ ሕዝባችን ላይና በተለይም በገጠሩ ሕዝብ ትልቅ ቀውጢ ፈጥረው ውለዋል፣ ይህንንም በምርጫ እለት የአፈና ዘመቻ በመፈፀም አመቺ ሁኔታን አመቻችተዋል። ይኸውም የሀገር ውስጥ ሀቀኛ ታዛቢ

በሌለበት ዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ከአዲስ አበባ እንዳይወጣ በተከለከለበትና አውሮፓ ህብረት ታዛቢዎችም ከአዲስ አበባና ከሌሎች ዋና ዋና ከተማዎች መውጣት ፈርተው በየአሊቤርጎአቸው በመሸጉበት ሁኔታ ምርጫው እንዲካሄድ በኢህአዴግ መወሰኑ ነው፡፡

ስለሆነም ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓም የተከናወነው ክስተት ‹ምርጫ› ሳይሆን፣ ኢህአዴግ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ክብር ባለው ንቀት ያካሄደው ድራማ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ድምዳሜያችንም ብዙ እንቅስቃሴ ባላደረገው፣ በጥቂቱ ካየውና ከተመለከተው በመነሳት የአውሮፓ ህብረት ቡድን በደረሰበት ድምዳሜ የተደገፈ በመሆኑ፣ ትክክለኛ ነው እንላለን፡፡ ስለምርጫው ኢ-ዴሞክራሲያዊነት በውጭ ሀገር ታዛቢ ቡድን የተሰጠው ምስክርነትም በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲለመልም ሕይወቱን ጭምር እየሰዋ ለታገለው ሕዝባችን ትንሽ መጽናኛ ትሆነዋልች የሚል እምነት አለን፡፡

አዎን! ብቻችንን አይደለንም! ዓለም ይብዛም ይነስም በዴሞክራሲ ስም በኢትዮጵያ ሀገራትን የሚፈፀመውን ደባ አይቶታል! የመድረክ አባላትና ደጋፊ የሆኑ ዜጎችንም ድርጅታቸው ለህዝቡና ለሀገሩ የገባውን ቃል እውን ለማድረግ መስዋትነት መክፈል ሳይፈሩ ምርጫውን ሀቀኛ ለማድረግ፣ በየጣቢያ የተመደቡትና ተዘዋዋሪ ተወካዮቻችን በጽናት ታግለዋል፣ ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ላይ ባወጀው ጦርነት ውስጥም ተንቀሳቅሰው መድረክን ለድል ለማብቃት እልህ አስጨራሽ ትግል አድርገዋል፡፡ ለነዚህ ወገኖቻችን ያለንን አክብሮት በከፍተኛ ስሜት እንገልፃለን፡፡ ለኢህአዴግ መንግሥትም በየምርጫ ጣቢያው በተወካይነት የመደብናቸውን አባሎቻችንን እስካሁን ድረስም በማሳደድ በማስርና በሀሰት በመወንጀል፣ ከኑሯቸው ተፈናቅለው ስለሚገኙ ይህን የቂም በቀል እርምጃ በአስቸኪይ እንዲያስቆሙ በአንክሮ እንጠይቃን፡፡

ይህ በእንዲህ አንዳለ ከትናትናው የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤት እወጃና ከኢህአደግ መሪም ንግግር የምንረዳው በሀገራችን በመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ላይ ማእቀብ እንደተጣለ ነው እንጂ መድረክ ‹ተሸናፊ› ፓርቲ ነው የሚሉት አሳቤ በገጠርም ሆነ በየከተማው ያለው ሕዝባችን ከሰጠን ድምጽ ጋር የሚጣረስ ነው፡፡ ለዚህም ዋና አመልካች ‹የሕዝብ ድምጽ ይከበር› በሚል ኢህአዴግ ባዘጋጀው ሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይም ‹የሕዝብ ድምጽ ለአምስቱ የእጅ ጣቶች› መሆኑን ሕዝብ ሲያሳይ መዋሉን ልብ ይሏል እንላለን፡፡ ስለሆነም የዘረዘርናቸው የምርጫ

ሕግና የሥነ ምግባር ሕግ ጥሰቶች ሁሉ በታረሙበትና የሀገር ውስጥና የውጪ ታዛቢዎች በስፋት የተሰማሩበት ሁኔታ ምርጫው መድገም አለበት የሚል ጥብቅ አቋም አለን።

በመጨረሻም መድረክ ከሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ የትግል ጎዳና ዝንፍ ሳይል በግንቦት 15ቱ የምርጫ አፈና ከከፈተበት የኢህአዴግ ሥርዓት ጋር እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ ገብቶ በመረጠው ሕዝብ ታጅቦ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በሀገራችን እውን ለማድግ ከምን ጊዜም በላይ ቆርጦ እንደሚታገል ለመላው ሕዝባችንና ለአለም አቀፍ ዴሞክራሲያዊ ሀገሮች ሁሉ ማሳወቅ እንወዳለን!

## የአንድ ፓርቲ ፍፁማዊ የበላይነት አገዛዝ ያከትማል

## ድል ለመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት!

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ

ግንቦት 18 ቀን 2002 ዓም